የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ- ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 39
ADDIS ABABA- 26st May. 2005

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፩/፲፱፻፺፯ ዓ.ም**

በመረጃ እና በመገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...ገጽ ፫ሺ፩፻፲፭

## CONTENTS

**Proclamation No. 451/2005**

International Development Association Credit Agreemer for Financing Information and Communicatio Technology Assisted Development Project Ratificatio Proclamation ........ Page 3115

### አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፩/፲፱፻፺፯

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ ልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በመረጃ እና በመገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፯ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (አሥራ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፬ ቀን ፪ሺ፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በመረጃ እና በመገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፩/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### PROCLAMATION NO. 451/2005.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEVELOPMENT CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 17,100,000 SDR (seventeen million one hundred thousand SDR) for financing Information and Communication Technology Assisted Development Project, was signed in Washington DC on 4th day of January, 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal democratic Republic of Ethiopia has ratified said Development Credit Agreement at its session held on the 26th day of May, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Information and Communication Technology Assisted Development Project Ratification Proclamation No. 451/2005."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢ.ት የጵ.ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፬ ቀን ፪ሺ፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር 3985ET የብድር ስምምነት ነው::

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፯ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (አሥራ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Definition

In this Proclamation "Development Credit Agreement" means the Credit Number 3985ET signed in Washington DC on the 4th January 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 17,100,000 SDR (seventeen million one hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Development Credit Agreement.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on the 26th day of May, 2005.

Done at Addis Ababa, the 26th day of May, 2005

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት